# ዋይታ

Waytta@gmail.com

ቅጽ 1 ቁጥር 1 ታህሳስ 1/2003

**ሀገራችን ሲያፈራርሷትና ወገናችን ሲያሰቃዩት እያየን ጥርስ ከመንከስ ይልቅ**

**ተባብረን በወያኔ የሚፈፀምብንን በደል ለማስወገድ በጋራ እንንሳ።**

የህዝብን መብትና ድምፅ የማያከብር መንግስት ተብዬ መጨረሻ አወዳደቁ እንደማያምር ከተለያዩ የዓለም አምባ ገነን መሪዎች በተደጋጋሚ የሚታዩ ክስተቶች ናቸዉ ። ሥለዚህ በኢትዮጵያችን እየሆነ ያለዉም የዚሁ ዉጤት ሰለባ ነዉ ። በሰለጠነ መንገድ ከህዝብ ድምፅ አግኝቶ አገርን በሰላም ያለ ሰቀቀን ከመምራት ይልቅ የጠመንጃ ቃታን በመተማመን ሕዝብን ሳይወድ በግድ አምበርክኮ ለመግዛት መጣሩ አንድም የአዕምሮ በሽተኛ ካልሆነ በስተቀር የሚያስብ ጭንቅላት ያለዉ ፍጡር የሚከተለዉ አማራጭ መንገድ አይደለም ምክንያቱም የማታ ማታ አሸናፊዉ ሕዝብ ነዉ እና። ከዉጥኑ ጀምሮ እስከ አሁን ያልተቀየረዉና የዉስጥ ለዉስጥ የወያኔ የድርጊት መመርያ ሆኖ የሚያገለግለዉ የየካቲት 1969 ዓ.ም "**የወያኔ ማኒፌስቶ**" እንዳስቀመጠዉ የወያኔ የመጨረሻ ግብ "**ታላቋ የትግራይ ሪፓብሊክን**" ለትግራይ ሕዝብ ሳይወድ በግድ እዉን ማድረግ ነዉ።

**ይህን አላማ ከግቡ ለማድረስ ወያኔ የወሰደቻቸዉ እርምጃዎች፤**

**1ኛ/ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቋማትን አፍርሶ ወይንም አጥፍቶ በምትካቸዉ በዘርና በጎሳ ባማከለ ብቃትና ችሎታ በሌላቸዉ የወያኔ የፖለቲካ ካድሬዎች የሚመሩ ለሀገሪቱ ሳይሆን ለወያኔ የበላይ አመራር አካላት ብቻ ተጠያቂና ታማኝ የሆኑ አዲስ ተቋማትን መፍጠር።**

**ለምሳሌ፦** ከሃምሳ አመታት በላይ በጀግንነቱና በህግ አስከባሪነቱ በሞያዉና በወታደራዊ ስነ ስርአቱ በዓለም ታዋቂነት የነበረዉን የሀገሪቱ መከላከያ ኋይል ተቋም (ያየርና የባህር ኋይል፣የምድር ጦርና የፖሊስ ሰራዊት) የደርግ ሰራዊት ነዉ በሚል ሽፋን ይህን ጠንካራ ህብረ ብሔር የሰለጠነና የተማረ ስብስብ አፍርሶ በመጣል የሙያ ብቃትም ይሁን በቂ ወታደራዊ ትምህርትና ሥነስርአት በሌላቸዉ በአንድ ዘር ሃረግ (ትግራዋይ) የሚመራና የተመሰረተ የሃገሪቱ ሳይሆን የወያኔ ደህንነትን የሚያስጠብቅና እርስ በርሱ የማይተማመን ደረቅ ጦር በመፍጠር ሀገሪቱ ለጎረቤትም ይሁን ለማንኛቸዉም ጥቃት በቀላሉ አጋልጦና አመቻችቶ ማስቀመጥ ነዉ።

2ኛ/ ሀገሪቱ በልመናም ይሁን በከፍተኛ ወጭ ሃገር ዉስጥና በዉጭ ዐለም አስተምራ ያደረሰቻቸዉን ታዋቂ ምሁራንና የዩኒቨርስቲ ሊቃዉንት ያላንዳች በቂ ምክንያት ከሚያስተምሩበት የትምህርት ገበታ በማስወገድ በምትካቸዉ በከባድ ምንዛሪ ብቃት የሌላቸዉን የዉጭ ሃገር መምህራን መቅጠር።

3ኛ/ በኤርትራም ይሁን በመላ ኢትዮጵያ ያለዉ ሕዝብ የኤርትራን በራስ የመወሰን ጉዳይ ሳይወያይበትና ሳይመክርበት በወያኔና በሻዕቢያ የደደቢት የበረሃ ዉል መሰረት ለግብፃዊዉ ብትሮስ ጋሊ (የተባበሩት መንግስታት የወቅቱ ዋና ፀሀፊ) ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የድጋፍ ደብዳቤ በመላክ የኤርትራ ሪፈረንደም **"ባርነት ወይንስ ነፃነት"** በሚል እልክ አስፈጅ ምርጫ በማድረግ እናት ሀገር ኢትዮጵያ ዐይኗ እያየ አንዱን ልጇ እንድትነፈግና ዳር ደንበሯን እንድትነጥቅ ማድረግ።

4ኛ/ የዓባይ ወንዝ ባለቤትነታችንና ተጠቃሚነታችን አስመልክቶ ይህ የወያኔ ቡድን በአባይ ተፋሰስ አገር ዙሪያ የሚያደርገው የይስሙላ ጩኸትና የድረሱልኝ ሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ሀቁን በመደባበቅ አሁንም የተለመደ ያታላይነት አክሮባቱን እየሰራብን ነው፤

 ሀ) ከ100 አመታት በፊት ቅኝ ገዥዎች ባስቀመጡት ኢትዮጵያን ቀፍድዶ የያዘ ያለግብጽና ሱዳን ፈቃድ ሀገራችን በአባይ ወንዝ ምንም አይነት የስራ ፕሮጀክት መስራት በማያስችላት ውል፣ ግብፅና ሱዳንን በሚጠቅም የተስማማ፤

ለ) ወያኔ ለግብጾች የአባይን ወንዝ መቆጣጠር እንድያመቻቸው፣ በአባይ ወንዝ ማመንጫ አናት ላይ በባህርዳር ከተማ አካባቢ ሰፊ መሬት ለረጅም ዘመናት በሚቆይ ሊዝ የሰጠ፤

ሐ/ በአባይ ወንዝ ሽፋን በቅርቡ ወያኔ በዋሽንግቶን ዲ.ሲ. ያካሄደው የይስሙላ ሰላማዊ ሰልፍ ብዙ የዋሆችን ያታለለ በርግጥ ለሃገር ትቅም ያሰበና የአባይ ወንዝ ጉዳይን ያማከለ ሳይሆን የአምባገነኑ የመለስን እድሜ እንዲራዘምና የፖለቲካ ድጋፍ ለመስጠት እንደነበር መሆኑ እየታወቀ ሆኖ እያለ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና ለህልዉናዉ የሚያደርገዉን ትግል ለማዳከምና አቅጣጫዉን በማስቀየር ትግሉ ግቡን እንዳይመታና የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም እንጅ የሚያስገኘዉ ጥቅም አይኖርም።

5ኛ/ በሃገሪቱ ዉስጥ የግልም ይሁን የመንግስት የነበሩትንና አሁንም በርዳታ የሚገኙትን ተሽከርካሪዎች፣ የኢኮኖሚ መገንብያና የማምረቻ መሳርያዎች ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ በጠቅላላ በመንግስት ስም ለወያኔ ዉርስ በማድረግ በነዚህ መስርያ ቤቶች ለረጅም ጊዜ ይሰሩ የነበሩ ሰራተኞችንና ረጅም ልምድ ያላቸዉን በግምገማ ሰበብ ከነሱ ዘር ያልተፈጠሩና የትግራይ ዘር ካልሆኑ በስተቀር ከስራ ማሰናበትና ማባረር በምትካቸዉ የወያኔ አባላትና ደጋፊዎችን በማስቀመጥ የነባር ቀዳሚ ሰራተኞችን ሀገራዊ ፍቅርና ኢትዮጵያዊነታቸዉን እንዲጠሉና ወያኔ በፈጠረዉ የፖለቲካና የዘር ሹኩቻ እንዲበከሉ ማድረግ።

6ኛ/ በማህል አገር ዉስጥ በስፋታቸዉና በለምነታቸዉ እንዲሁም ለአምራቹ ገበሬ አመች የነበሩትን መሬቶቹንና ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ለማጥፋት ሌት ተቀን ለሚጥሩ ጠላቶቿ በአጭር ጊዜ ሊፈርስ በማይችል ሊዝ በባሕርዳርና በአፋር ለግብፅ (የዓባይን ምንጭ ለመቆጣጠርና የሃይማኖት ግጭት ለማስፋፋት) እንዲሁም በሌሎች በኢትዮጵያ ግዛቶች ከትግራይ በስተቀር ለሳዉዲ አረብያና ለክዌት አረብ አገሮችና ለሌሎችም መቸርቸር ወይንም መስጠት።

7ኛ/ የሃይማኖት እኩልነት በሀገሪቱ እንዲሰፍን የወያኔ መንግስት የበኩሉን እርዳታ ከማድረግ ይልቅ፥

ሀ/ በሃገር ዉስጥ የቆዩትንና ህዝቡ የሚያምንባቸዉ ተቋማት ወያኔ በአንድ ዘር የበላይነት በሚመሩና በፖለቲካ ካድሬዎቹ ስልጣኑን በማስያዝ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን ማፍለስ፣ የቤተ ክህነት ሊቃዉንትን፣ የበቁ ጠበብትንና መነኮሳትን ከሃገር በማባረር ተቋሙን ማዳከምና ማፈራረስ፤

ለ/ የእስልምናዉን ህብረተሰብ በሳዉዲ አረብያና በኢራን በሚደገፉ ወሃቢ መድረሳዎች አማካኝነት የወጣቱ ክፍል የአባትና የቅድመ አያቶቻቸዉን እምነት ማጣጣል፣ መዝለፍ፣ መሳደብና የአክራሪነትን አቋም እንዲከተሉ መፍቀድና በስተጀርባ ድጋፍ መስጠት፤

ሐ/ የእምነቱን በር የበለጠ ለመጤና ለባእድ ሃይማኖቶች አመቻችቶ በመክፈት የወጣቱን ትኩስ አእምሮ በመጤ ሃይማኖት ወጥመድ ዉስጥ በማሰር ከቅርብ ሆኖ መበላሸቱን በይበልጥ መገፋፋት፤

መ/ ለዘመናት ተቻችለዉና ተከባብረዉ በኖሩት በእስላምና በክርስትያን ሃይማኖቶች መካከል በሰበብ አስባቡ የርስ በርስ የሃይማኖት ብጥብጥና ግጭቶችን መፍጠር።

8ኛ/ ወያኔ ጠንካራና የተማረ ታሪክና ትዉልድ ተረካቢዉን ወጣት ዜጋ ከመፍጠር ይልቅ በተበላሸ የትምህርት ፖሊሲ ዉስጥ በመዘፈቅ በዘር ፣ በጎሳና በጎጥ በመከፋፈል፡

ሀ/ በመጤና በባእድ  ሃይማኖት ማቅ ዉስጥ ገብቶ ተገዥ እንዲሆን፣

ለ/ በሲጋራ፤ በጫትና ባልተለመዱ አፍዛዥና አደንዛዥ እፆች እንዲለከፍ፣

ሐ/ በመጠጥ ቤት ደንበኝነትና በዳንኬራ ቤት አባልነት ጊዜውን በከንቱ እንዲያሳልፍ፣

መ/ የስራ መስክ ባለመኖሩ ወጣት እህቶች በሀገር ቤትም ይሁን በአረብ አገሮች ዉሉ ባልተገለፀ ሰነድ በሴተኛ አዳሪነት ስራ ማሰማራትና ባልታወቀ በሽታ በመለከፍ በለጋ እድሚያቸዉ ማስቀጨት፣

ሠ/ ወጣቶችን ሥራ ዉጭ አገር ተገኝቶላቹኋል በማለት በባርነት ለአረቦች መሸጥ፤

ረ/ የወደፊት ታዳጊ የሃገሪቱን ልጆች በጉደፈቻ ለምእራባውያን ፈረንጆች በብዙ ዶላር መለወጥ።

9ኛ/ ከጋምቤላ፣ ወለጋ፣ ጎጃምና ጎንደር የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ሁለገብ መሬት ለብዙ ዘመናት በኢትዮጵያዊያን ባለቤቶቹ፣ ድንበር ጠባቂዎችና ጭቃ ሹሞች ሲጠበቅ የኖረዉን መሬት እርዝመቱ 1632 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ከ30-60 ኪሎ ሜትር ለሱዳን ለማስረከብና መስመር ለመከለል ሕዝቡን ሳያማክሩ በዝግ ስብሰባ ዉሎችን መፈረም።

10ኛ/ ለሃገራችን ጎጅና አጥፊ በሆኑ ዉሎች ላይ ያለአግባብ በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ፊት በመዋዋል ሀገሪቱ ሰላም መረጋጋት እንዲሁም ዳር ደንበር ያላት ሀገር ከማድረግ ይልቅ ዜጎቿ የማይስማሙ በዘር በጎሳና በነገድ የተለያዩ በጣም ደካማና ትንሽ ድሃና በእርዳታ የምትኖር ሀገር መፍጠር አለበለዝያም ሀገሪቱን ማጥፋትና እንዳትኖር ማድረግ፤

11ኛ/ በየግዜዉ እርስ በራሳችን የምንጨቃጨቅበት አጀንዳዎችን በመፍጠር የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠበቅበትን የጋራና የአንድነት ትግል እንዳይፈጥር እንቅፋት መሆን፤

12ኛ/ የትግራይ ክፍለሃገር የመሬት ስፋት ወይንም ይዞታ ከ65000 ወደ 102000 ስኴር ኪሎሜትር ማሳደግ። ይህም በምእራብ ከጎንደር (ሁመራ፣ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት) በደቡብ ከወሎ (ኣላማጣ፣ አሸንጌና ቆቦ) እንዲሁም በምስራቅና ሰሜን ኩናማ፣ ሳሆ፣ አፋርና አሰብን ጨምሮ ሲሆን ታላቋ ትግራይ በየብስ ከዉጩ ዓለም ለመገናኘት ከጎንደር በተወሰዱት አመካኝነት በሱዳን በኩል ሲሆን በባህር ደግሞ ከአፋር ለወደፊቱ ከሚወስዱቸዉ የአሰብ ወደብና በሌሎች በቀይ ባህር ወደቦች መጠቀም ሲሆን ባየር በኩል ቢሆንም የሌላ መንግስት ፈቃድ ሳይጠይቁ በዚሁ በቀይ ባህር በኩል ለመጠቀም ነው። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ትግርኛ ተናጋሪዉን በድሮ ትግራይ ክፍለ ሀገር የሚኖረዉን ብቻ ሳይሆን አሁን መንግስት ከሆኑ በኋላ ከጎንደር አማሮችን፣ ከወሎ አገዎችን፣ ከአፋር አፋርኛና ከሳሆ ሳሆኛ ተናጋሪዎችን በአንድ በመጨፍለቅ ትግርኛ ተናጋሪዎች ናቸዉ በማለት ነዉ።

ወያኔ ስልጣን ከያዘች ከ1991 አ.ም ጀምሮ በጉልበት ያለ ህዝብ ፍላጎት ከጎንደርና ከወሎ በተወሰዱት ቦታዎች አካባቢ የሚኖረዉ ህዝብ በወያኔዎች የሚደርስበት የዘር ማጥፋት ወንጀል በከፊሉ ለመግለፅ ያህል፣

ሀ/ ብዙ እዉቀትና ልምድ ያላቸዉን ታሪክ አስተማሪ አገር ወዳድ አርበኞችንና የተከበሩ አዛዉንቶችን ከቤቶቻቸዉ ለቅመዉ በመዉሰድ ደበዛቸዉ ማጥፋት፤

ለ/ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የእነዚህ አካባቢ ነዋሪዎችንና ጀግኖችን በየምክንያቱ እስከነሕይወታቸዉ በሰዉ ሰራሽ ጨለማ ጉድጓድ ዉስጥ በማሰር፦

- .ብርሀን በማጣት አይናቸዉ እንዲታወር፣
- .ምንም አይነት እንቅስቃሴ በእስር ቤቱ ባለመፍቀድ ሰዉነታቸዉ በሙሉ እንዲዳከምና በተለያዩ በሽታዎች እንዲጠቁ ማድረግ፣
- .ሰዉነትም ሆነ ልብስ መታጠብ ባለመኖሩ ታሳሪዎቹ ሰዉነታቸዉ ንፅህና በለለዉ ጉድጓድ በሚፈጠረዉ ቆሻሻና ተባይ ተልቶና ሚሸሸ አይናቸዉ እያዩ እንዲሞቱ ማድረግ።

ሐ/ የጎንደር የልማት ምሶሶ የሆኑትን እጅግ ለም መሬቶች በጉልበት ነጥቆ በመዉሰድ (ወልቃይት ጠገዴ ሁመራና ጠለምት) ከአምስት መቶ ሺ(500,000) በላይ የትግራይ ተወላጆችን በቦታዉ አስፍሮና ወደትግራይ መቀላቀሉ አልበቃ ብሏቸዉ አሁንም ከአርማጭሆ እስከ መተማ ባለዉ ለም መሬት (ሱዳን ጠረፍ) የአገሬዉን ገበሬ በማፈናቀል የትግራይ ገበሬዎች እያሰፈሩበት ነዉ።

መ/ ባልረባቡ ምክንያቶች እጅግ ከፍተኛ ቅጣቶችን በሕዝቡ ላይ በመበየን ዓይን ያወጣ የንብረትና የገንዘብ ዘረፋዎች ማካሄድ።

ሠ/ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የጎንደር (የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት) እና የወሎ ተወላጅ ኢትዮጵያዉያን እህቶች ሳይወዱ በግድ ተገደዉ ከወያኔ ወንዶች እንዲወልዱ በማድረግ የነበረዉን ትዉልድ ዘር አጥፍተዉ በራሳቸዉ አዲስ ዘር በመተካት ለዝንተ ዓለም የኖረዉን የነዚህ አካባቢ ታሪክ ለማጨለምና ጨርሶ ለማጥፋት የባህል፣ የህሊና ተፅዕኖ፣ የቋንቋና፣ ማህበራዊ ኑሮ (ዲሞግራፊ) እንዲቀየር ማድረግ።

<u>ለምሳሌ፦</u> ድሮ በኢትዮጵያዊ ቀለም ተዠጎርጉራ የነበረችዉ የሁመራ ከተማ ዛሬ 99.9% የትግራይ ሰዉ ብቻ መኖርያ ሆናለች። እንዲሁም የወልቃይት መዘጋ፣ አዲጎሹ፣ ባህከርና ዳንሻ የመሳሰሉት ለም መሬቶች መቶ በመቶ ነዋሪዉ የትግራይ ሕዝብ ብቻ የሆነበት ሁኔታ ነዉ የተፈጠረው።

*ረ/ መጠኑ እጅግ የበዛ ሕዝብ ቦታዉን ለቆ ወደ ባእድ አገር እንዲሰደድ ማድረግ፣ ከእስራት፣ ከሞትና ከስደት የተረፈዉ ቀሪዉ ሕዝብ አርሶ ቤተሰቦቹን እንዳይመግብ መሬቱን ቀምተዉ በድህነት ፍዳዉን እያሳዩት መኖር ስላንገበገበዉ ብሶቱን ያለ ፍርሀት መግለፅ ስለጀመረ፣ ይህ ብሶት በሕዝቡ መሀል ከተስፋፋ አመፅ ሊቀሰቀስባቸዉ እንደሚችል የተገነዘቡ የወያኔ ባለስልጣናት በየጊዜዉ ወቅታዊ ስብሰባ በማድረግ የሚከተሉት ማታለያና መደለያዎች በተግባር ለማዋል በመስማማት፤*

- *የወልቃይት ጠገዴ፣ ሁመራና ጠለምት እንዲሁም የአላማጣ፣ አሸንጌና ቆቦ ጉዳይ ፈፅሞ ሊዳፈንልን ባለመቻሉ አንዳንድ ማታለያ ነገር ቃል በመግባት በተስፋ እንዲኖሩ በማድረግ አቅጣጫቸዉን ማስለወጥ፣ ጎንደሬ፣ ወሎዬ ነን የሚለዉን አመለካከታቸዉን ማስቀየር። አንዳንድ ከወያኔ ጥቅሞች ጋር የሚሄዱ ስራዎች እየሰራን ታማኝነታችንን ማሳየት ለምሳሌ፦ የአዉራ ጎዳና መንገድ ስራዉ እንዲጀመር ማድረግና ካድሬዎቻችን የሚያዙበት ትምህርት ቤት በማሰራት አካባቢዉን አጥብቆ መቆጣጠር።*

- *የወልቃይት ጠገዴ፣ ሁመራና ጠለምት እንዲሁም የአላማጣ፣ አሸንጌና ቆቦ ነዋሪዎች ጎንደሬና ወሎየ ነን ብለው ከሚያምኑ ይልቅ በመንደር እንዲደራጁ በመወትወት በጎንደርና በወሎ ሕዝብ ዐይን እንዲጠሉ ማድረግና ቅራኔ በመካከላቸዉ እንዲስፋፋ ጠንክሮ መስራት። ከጊዜ በሁዋላ ሳይወዱ በግድ ከመዳፍ ስራችን መግባታቸዉ የማይቀር ስለሆነ ለጊዜዉ ግን ለዘብ ማለት ይኖርብናል ይህ ስንል የህቡኡ ስራችን እርምጃ ከመዉሰድ እንቆጠብ ማለታችን አይደለም። በዚህ አካባቢ የሚሰጠዉ የትምህርት አሰጣጥም ስለ ትግራይ የበላይነት የሚያንፀባርቁ ቅስቀሳዎች ተማሪዎች እንዲቀስሙ ማድረግ እንጅ ሌላ ነገር ስለ ኢትዮጵያ ሀገራዊነት እንዲያዉቁ አለማድረግ። የህዝቡ የአኗኗር ሁናቴም አሁን ካለበት አንድ ስንዝር ወደፊት እንዲራመድ አለማድረግ ለምሳሌ፦ ወጣቱ ስለመብቱና ስለነፃነቱ እንዳያስብ የተለያዩ የአፍዝዝ አደንዝዝ እፆች ብብዛት በአካባቢዉ እንዲኖሩ ማድረግና የመጠጥ ሱሰኞች እንዲሆኑና በአባ ወራዎቹም ላይ ያለ አቅማቸዉ ከባድ ቀረጥ በመጣል በድህነት አሮንቋ በመዘፈቅ ለአመፅ እንዳይነሳሱ ማድረግ።*

- *ከጎንደርና ከወሎ ከተወሰዱ መሬቶች ነዋሪዎች መካከል በተቃዋሚ ፖለቲካና በሀገር ወዳድነት ሊሰለፉ የማይችሉትን አንዳንድ ጥቅም በመስጠት ለወያኔ ታማኝ አገልጋዮች እንዲሆኑና እነዚህ ግለሰቦች በህዝቡ መሀል እንዲሰማሩ በማድረግ የሚቃወሙንና የሚጠሉንን ለእኛ በመጠቆም በስለላ ተግባር እንዲያገለግሉን ማድረግ።*

- *ጠላቶቻችንን በረቀቀ ዘዴ ከአካባቢዉ ማፅዳትና የትግራይ የበላይነትን ላንዴም ለመጨረሻም ማረጋገጥ፤*

- *ልማት የሚለዉ የተስፋ መፈክራችን እንዲስፋፋና የመብት የፍትህና የነጻነት ፓለቲካዊ ጥያቄ አቅጣጫዉን ለማስቀየር፣ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን የእድገት እንቅፋት እንደሆኑ አስመስለዉ የሚያጋልጡልን ለወያኔ ታማኝ የሆኑትን ምሁራን በመጋበዝና ደጎስ ያለ ጥቅም በመስጠት የአብዮታዊ ዲሞክራሲን መርህ ማጠንጠንና ልክ እንደ ቻይና መንግስት ራሳችን በበለጠ ማጎልበት።*

***<u>ወያኔዎች ጎንደርን ለማዳከምና ረግጦ ለመግዛት የወሰዱቸዉ እርምጃዎች፤</u>***

***1ኛ/*** *የጎንደር የልማት ምሰሶ የሆኑትን እጅግ ለም መሬቶችን በጉልበት ሲነጥቁ፣ ጣልያን ተክሏት የሄደዉ አንዲት አሮጌ የመብራት ኋይል ማመንጫና የነዳጅ ማጠራቀምያ ቦቴዎችን ስልጣን በያዙ ጥዋት ነቅለዉ ሲወስዱ የከፋቸዉ የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች በወቅቱ ይህን አንጎራጉረው ነበር፤*

*ጣልያን የተከለዉ የኮረንቲዉ ሞተር፣*

*የኋይል ማመንጫችን የኤሌክትሪክ ሰፈር፣*

*ጀግና በማጣቱ ተነቀለ ጎንደር።*

2ኛ/ *ታሪካዊና ለም የሆኑትን መሬቶቻችን ከሁመራ እስከ ጋምቤላ አፄ ቴድሮስ የተወለዱበትና አፄ ዮሃንስ የተሰዉበትን ጭምር ለጊዚያዊ ጥቅማቸዉ ሲሉ ለሱዳን አሳልፈዉ ስለሰጡት፣ የሱዳን ሰራዊት ወያኔን መከታ በማድረግ የጎንደርን ግዛቶች በተደጋጋሚ ጥሶ በመግባት በቋራና በነፍሶ ገበያ እርሻ ቦታ ተሰማርተዉ የነበሩትን ከ*30 *በላይ ኢትዮጵያዊያን አስሮ፣ ጠቅላላ ንብረታቸዉን አቃጥሎና ዘርፎ ሲወስድ የወያኔ መሪ መለሰ ዜናዊ ተጠይቆ በመካድ **"ማንም የተፈናቀለና የታሰረ የለም አይኖርምም"** በማለት የሱዳን ጠበቃነቱን አረጋግጧል።ታድያ በቆራጥ ወገኖቻችን ትግልና መስዋእትነት የታሰሩት ሲፈቱ የጠፉ ወገኖቻችንና የተዘረፉ ንብረቶች ግን ሳይመለሱ ቀርተዋል። ያገሬዉ ሰዉ መሬቱንና ንብረቱን ለማስመለስ ላደረገዉ ጥረት በወያኔና በሱዳን ጦር ተባባሪነት ተደብድቧል። ይህን በሚመለከት የኢትዮጵያ ደንበር ኮሚቴ ተከታታይ መግለጫዎችን አዉጥቷል። በአንፃሩ የሱዳን መንግስት በሃገሩ የወያኔን ተቃዋሚ ሃይሎች እንቅስቃሴ እንዳይኖር ማድረግና ወያኔ የሚፈልጋቸዉን ስደተኞችም አፍኖና አስሮ ለወያኔ አስረክቧል። <u>ለምሳሌ፣</u> የ*80 *ዓመቱ አዛዉንት ሻለቃ አጣናዉ ዋሴ በእስር ላይ እንዳሉ ሕይወታቸዉ እንዳለፈ የሚታወስ ሲሆን እንደነ ሻለቃ ጌታቸዉ ይርጋና ሌሎቹ ስማቸዉ ለጊዜዉ ያልተዘረዘሩት ስደተኞች ከሱዳን ታፍነዉ ደበዛቸዉና መዳረሻቸው እስከአሁን እንደጠፉ ነዉ።*

3ኛ/ *የተሻለ ትምህርትና ሞራል የትግራይ ወጣት እንዲያገኝ ሲደረግ ሌላው የሃገሪቱ ወጣት ግን እንዲኮላሽ፣ ቅስሙና ሞራሉ የተሰበረ የወደፊት ሃላፊነቱን መረከብ እንዳይችል የስነ ልቦና ዝግጅቱ እጅግ ደካማና ተስፋ ቆርጦ እየፈራና እየተጠራጠረ ኑሮውን በተገዥነት ማስገፋት።*

4ኛ/ *ወያኔ ስልጣኗንና ጥቅሟን ለማስጠበቅ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በሃገርም ሆነ በተለይ በዉጭ ዓለም የሚገኘዉን ወገን በተለያዩ መደለያ መሬት ይሰጥሃል፣ ንግድ ይፈቀድልሃል ካፒታል በገፍ ይቀርብልሃል ወዘተ. በማለት የውሸት ተስፋ በመስጠት ቢቻል የወያኔ ደጋፊዎች እንዲሆኑ ባይቻል ደግሞ በተቃዋሚነት እንዳይሰለፉ ማድረግ።*

*ይህ ከአንድ ጎሳ የተውጣጡ ጥቂት ዘረኞች የፈጠሩት የወያኔ ቡድን ለግል ጥቅምና ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብቻ ቆሜለታለሁ ለሚሉት የትግራይ ሕዝብንም እንኳ፣*

ሀ/ *በ*1975 *ኢ.ም በድርቁና በረሃቡ ምክንያት የትግራይን ሕዝብ በእግሩ ቤቱንና ቀየዉን እየለቀቀ እስከሙሉ ቤተሰቡ ወደ ሱዳን እንዲሰደድ በማድረግ ከ*13000 *በላይ ሰዎች በድካምና በተላላፊ በሽታ፣ በርሃብና ውሀ ጥም አስፈጅተው ከበጎ አድራጎት ድርጅት መለመኛ በማድረግ የተገኘውን እርዳታ ለተጎጂ ህዝብ መርጃ ከማድረግ ይልቅ በቅድሚያ ለድርጅታቸው ጥቅም ያዋሉ፤*

ለ/ *ከደርግ መረጃ ጋር ሁኔታዎችን በማመቻቸት ምስኪን የትግራይ ሕዝብ በሀውዜን ከተማ ገቢያ እያደረገ ባለበት ቅዳሜ ቀን በደርግ አይሮፕላን ድብደባ ህዝብን ያስጨፍጨፉ፤*

ሐ/ የሻእብያን የመገንጠል ትግል የትግራይ ወጣቶች ሳያምኑበት የትግል አጋራችንን እንርዳ በማለት ብዙ የትግራይ ወጣቶች ወደ ኤርትራ በመላክ በቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ ያስፈጁ፤

መ/ በ TLFና በ TPLF መካከል እርቅ ወርዱል ብሎ ወያኔ በይፋ ለአባላቱ ከነገረ በኋላ በነመለሰ የሚመራዉ ወያኔ ክፍል የቀድሞ TLF አባላትን ሌሊት እንደተኙ የረሸኑና ያረዱ፤

ከዚህና እነዚህን ከመሳሰሉት ያለፉት የወያኔ ተግባሮቻቸውና አሁንም በግልጽ፣ በደባና በድብቅ በሚሰሩት ከምናየውና ከምንሰማው ብንነሳ በምን ስሌት ይሆን ለኢትዮጵያ ሀገራዊነት የሚያስቡት። ይህችን ደካማና ጎስቋላ ሃገር ጠብቃዉና ተንከባክባው የቆዩቾዉን መሬቷንና ዳር ደንበሯን የቆራረሱ፣ ከሌላዉ ዓለም ጋር በባሕር የሚያገናኛትን ወደቧን ያሳጡ፣ ሰፋፊና አንጋባች የእርሻ መሬቷን ልኩ ባልታወቀ የዝግ ስብሰባ ለሱዳን በገፀ በረከት የሰጡ፣ በመሃል ሀገር ውስጥ ህዝቡ አርሶ የሚጠቀምበትን ሰፋፊ ለም መሬት አሳልፎ ለዘመናት ጠላቶችዋ በአጭር ጊዜ ዉስጥ በማይፈርስ ሊዝ የሸጡ ወዘተ… ከዚህ በኋላ ምን እስክንሆንና ምን እስኪፈጠር ነው የምንጠብቀው? ከብዙ በጥቂቱ እንኳን የተገለጹት ካላሰባሰቡንና መፍትሄውን በጋራ ካልፈለግነው መቸ ይሆን በአንድነት በጠላታችን ላይ የምንነሳው?

**ደንበራችንን ለማስከበር፣ መብታችን ለማስጠበቅ፣ ሕልዉናችንን ለማረጋገጥ፣ ጠንካራና ቀጣይ ትዉልድ ለመተካት ተደራጅቶ መታገል አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው!!!**

**ከዋይታ**